በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የከተማ ልማት ቤቶች እና ኮንስትራክሽን ቢሮ

The Amhara National Regional State
Urban Development Housing & Constraction Bureau

ቁጥር ክልቤኮ-መሬ-04/180
ቀን 17/09/2009

ለ 3ቱ ክተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት
በፅኩ በት

ለ 10ሩ ዞን ከተማ ልማት ቤቶች፣ኮንስትራክሽን መምሪያ
በፅኩ በት

ጉዳዩ፡- **የመምህራን መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥ ደንብ ስለመላክ፤**

ክላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በክልሉ ውስጥ በመንግሥት ተቋማት እያገለገሉ የሚገኙ መምህራን የመኖሪያ ቤት ችግር በዘለቂታነት በመፍታት የተረጋጋ የመማር ማስተማር እንዲኖር ለማድረግ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ጥረት እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የፀደቀው የመንግሥት ተቋማት መምህራን የመኖሪያ ቦታ አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 150/2009ን ስካን በማድረግ በኢ-ሜል አድራሻችሁ የላክን ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሁሉም ከተሞች እንዲሰራጭ በማድረግ ለተፈፃሚነቱ ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር
ኢሳይ አቡ
ም/ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ
- ለቢሮ ኃላፊ
- ለም/ቢሮ ኃላፊ (ኮንስትራክሽን ዘርፍ)
- ለሕዝብ ግንኙነት ዋና የሥራ ሂደት
- ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና የሥራ ሂደት
- ለቤቶችና መሰረተ ልማት ዋና የሥራ ሂደት

ክልቤኮ ቢሮ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ትምህርት ቢሮ

Amhara National Regional
State Education Bureau

ቁጥር ---ገ፲ገ/፲፭፡፩/፳ገ

ቀን 14/9/2009

ለ---------- ዞን ት/መ/ጽ/ቤት

ጉዳዩ፡- የመም/የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሠጣጥ እና የተሠራ ቤት ድልድል ደንብ 150/2009ን ይመለከታል፤

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በክልላችን ውስጥ በመንግስት ተቋማት እያገለገሉ የሚገኙ መምህራን የመኖሪያ ቤት ችግራቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት የቤት መስሪያ ቦታ አሠጣጥ እና የተሠራ ቤት ድልድል ደንብ 150/2009ን ማፀደቁ ይታወሳል፡፡

በአሁኑ ወቅትም ህትመቱ ስለተጠናቀቀ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ ወረዳዎች ብዛት ---------- ለዞኑ ት/መ/ጽ/ቤት፣ለዞኑ ከተማ ልማትና ቤቶች ኮ/መምሪያ እንዲሁም ለ---------- መምህራን ት/ኮሌጅ ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ በድምሩ ------ ኮፒ የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ስዩም ደያግሱ ሻረው
ምክትል ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ፤

- ለቢሮ ኃላፊ፣ ጽ/ቤት
- ለም/ቢሮ ኃላፊ፣ (----------ዘርፍ)
- ለ---------- ዳይሬክቶሬት
- ለቢሯችን የህግ ባለሙያ

ትምህርት ቢሮ

- ለአብክመ ከተማ ልማትና ቤቶች ኮንስትራክሽን ቢሮ
- ለአብክመ መም/ማህበር

ባህር ዳር

ማውጫ ደንብ ቁጥር 150/2009 ዓ/ም	CONTENTS Regulation No. 150/2017
በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመምህራን የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥና የተገነቡ ቤቶች ድልድል ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	The Amhara National Regional State Teachers' Dwelling Houses' Construction Land Provision and the Distribution of Constructed Houses Execution, Council of Regional Government Regulation

ደንብ ቁጥር 150/2009 ዓ/ም	Regulation No. 150/2017
በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመምህራን የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥና የተገነቡ ቤቶች ድልድልን ለማስፈፀም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE EXECUTION OF THE TEACHERS' DWELLING HOUSES' CONSTRUCTION LAND DELIVERY AND THE DISTRIBUTION OF CONSTRUCTED HOUSES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

የመምህርነት ሙያ ዜጎችን በተገቢው እውቀት፣ ክህሎት፣ ቀና አመለካከትና በጎ እሴት የመቅረጽ ሀላፊነት ያለበት ከመሆኑም በላይ ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት ቁልፍ ሚና የሚጫወትና የህዳሴውን ጉዞ ለማሳካት የበኩሉን ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እንደሆነ በመታመኑ

Whereas, it is believed that the teaching profession, far from entailing a responsibility to shape citizens with the appropriate knowledge, skills, fair attitude and good values, would play a pivotal role for the multi-faceted development of our country and henceforth contribute its significant share to the successful accomplishment of the renaissance voyage;

የየደረጃውን መምህራን የመኖሪያና የመስሪያ አካባቢ የተመቻቸ በማድረግ ለአገር እድገት የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ ግዴታ በተነቃቃ መንፈስ መወጣት ይቻላቸው ዘንድ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች የተረጋጋ ስምሪት የሚኖርበትንና በዚህም አማካኝነት ጥራት ያለው ትምህርት የሚሰጥበትን እድል መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, it has been found necessary to create an opportunity in which the stabilized deployment of teachers shall exist and hence quality education shall be provided in all the localities of the region by facilitating their residential and working environment at all levels so that they would be able to discharge their professional duties in an activated spirit for the country's development;

በሙያው የለለጠኑና ብቃት ያላቸው የክልሉ መምህራን ከጊዜ ወደጊዜ ሙያቸውን እየተዉ ወደ ሌሎች የስራ መስኮች የሚያደርጉትን ፍልሰት ለመቀነስ ይቻል ዘንድ የመጠለያ ችግር በግል ሂወታቸው ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽእኖ በማስቀረትና ማህበራዊም ሆኑ ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን ከወዲሁ በማቃለል ቤተሰቦቻቸውና መላው ህብረተሰብ ለሙያው አዎንታዊ አመለካከት ኖሯቸው የየበኩላቸውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያደርጉላቸው የሚያበረታታ ራሱን የቻለ የህግ ማእቀፍ አውጥቶ ገቢራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

Whereas, in order that it might be possible to minimize the turn-over of those professionally trained and competent teachers in the region fleeing from their respective fields of profession in favor of other sectoral occupations from time to time, it is essential to enact and implement an autonomous legal framework that would somehow encourage their families and the society as a whole to provide them with their own support and care having thus developed a positive attitude for the profession in question, by getting rid of the problem which the lack of shelter happens to create in respect of their private lives and thereby alleviating their social and economic difficulties therewith;

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀፅ (7)ና በክልሉ አስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም አንቀጽ 37 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የመምህራን መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥና የተገነቡ ቤቶች ድልድል ማስፈጸሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 150/2009 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

ሀ. "መምህር" ማለት በክልሉ ውስጥ በሚገኝና ንብረትነቱ የመንግስት በሆነ ከቅድመ-መደበኛ እስከመሰናዶ 2ኛ ደረጃ ባለ ትምህርት ቤት፣ የመምህራን ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት፣ የግብርና፣ የጤና

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58 Sub-Art. (7) of the Revised National Regional Constitution and Art. 37 of the Revised Regional Executive Organs' Re-establishment, Organization and Definition of their Powers and Duties Proclamation No. 230/2015, hereby issues this regulation.

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short title

This Regulation may be cited as "The Teachers' Dwelling Houses' Construction Land Delivery and the Distribution of Constructed Houses Execution, Council of Regional Government Regulation No. 150/2017".

2. Definitions

1. Unless the context requires otherwise, in this regulation:-

A. "**Teacher**" shall mean any person who has been permanently recruited and serves in his profession as a teacher or trainer from pre-school through preparatory secondary level school, teachers' education, technical and vocational education, agriculture or health

ሳይንስ ኮሌጅ ወይም የአካል ተሃድሶ ማሰልጠኛ ወይም የአገልግሎት መስጫ ማእከል አስተማሪ ወይም አሰልጣኝ በመሆን በቋሚነት ተቀጥሮ በሙያው የሚያገለግል ማንኛውም ሰው ሲሆን፤ ርእሳነ-መምህራንን፣ ምክትል ርዕሳነ-መምህራንን፣ ሱፐርቫይዘሮችን፣ የየኮሌጆቹን ወይም የየማእከላቱን ዲኖች፣ ዳይሬክተሮችና ምክትሎቻቸውን ይጨምራል፡፡

science college or physical rehabilitation training or service delivery center found in the regional state and belongs to the government and may include principals, deputy principals, supervisors of such schools, deans, directors and their deputies of each and every college or center thereof.

ለ. "ትምህርት ቤት" ማለት በክልሉ ውስጥ ተቋቁሞ በመንግስት ይዞታ ስር የሚተዳደር ከቅድመ-መደበኛ እስከ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ያለ ማናቸውም ትምህርት ቤት ሲሆን የመምህራን ትምህርት፣ የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና፣ እንዲሁም የግብርና፣ የጤና ሳይንስ ኮሌጆችንና የአካል ተሃድሶ ማሰልጠኛ ወይም የአገልግሎት መስጫ ማእከላትን ይጨምራል፡፡

B. "**School**" shall mean any school set up in the Regional State and managed under the government ownership from preschool through preparatory secondary-level and include teachers' education, technical-vocational education and training, agriculture and health science colleges as well as physical rehabilitation training or service delivery centers.

ሐ. "የመምህራን መኖሪያ መንደር" ማለት ህጋዊ ባለቤትነቱ የክልሉ መንግስትና ህዝብ የሆነና የመምህራንን የመጠለያ ችግር ለመፍታት ታስቦ በመንግስት ወይም በመንግስትና በህብረተ-ሰቡ የጋራ ተሳትፎ የሚገነቡ ሆነው መምህራን በማስተማር ስራቸው ላይ እስካሉ ድረስ የሚጠቀሙባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያረፉበት ስፍራ ነው፡፡

C. "**Teachers' Residential Village**" shall mean a place whose lawful ownership is to the Regional Government and people and wherein condominiums to be constructed either by the government or through the joint participation of the government and the community with the intention of resolving teachers' shelter problem and used by teachers as long as they stay in their teaching career, are situated.

መ. "መኖሪያ ቦታ" ማለት በራሳቸው ምርጫ ገንብተው የሚጠቀሙበትን ቤት ለመስራት የሚያስችላቸውና በክልሉ መንግስት አማካኝነት በምደባ፣ በነፃ ወይም ካሳ ተከፍሎበትና በይፋ ተፈቅዶ ለመምህራን የተሰጠ ቦታነው፡፡

ሠ. "ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልገው መምህር" ማለት በፌደራሉ መንግስት የአካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 568/2000 ዓ.ም አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ስር የሚሸፈንና በሜዲካል ቦርድ የተረጋገጠለት አካል ጉዳተኛ ሆኖ የጉዳቱ ደረጃ በእኩል የስራ እድል ተጠቃሚነት መብቱ ላይ ተጽእኖ የሚያስከትልበት መሆኑ በአስፈጻሚ ኮሚቴው የታመነበት ማንኛውም መምህር ነው፡፡

ረ. (ንዑስ ማዘጋጃ-ቤት) ወይም (ታዳጊ ከተማ) ማለት እንደቅደም ተከተላቸው በአንድ መሪ ማዘጋጃ-ቤት ስር የተዋቀረ ከባቢያዊ የከተማ ማህበረ-ሰብ ወይም ማዘጋጃ-ቤት ያልተቋቋመበት ሆኖ ወደ ከተማነት በመሸጋገር ላይ ያለ ማናቸውም የማህበረ-ሰብ ስብስብ ነው፡፡

ሰ. "መሪ ማዘጋጃ-ቤት" ማለት በአንድ ወረዳ ውስጥ የሚገኙትን ንዑሳን ማዘጋጃ-ቤቶችና ታዳጊ ከተሞች በማእከልነት ይዞ ስራቸውን እንዲያስተባብርና በበላይነት እንዲመራ ሀላፊነት የተሰጠው ማዘጋጃ-ቤት ነው፡፡

D. **"Dwelling land"** shall mean that plot of land which has been granted to teachers by the Regional Government, upon its official approval, through allotment, free of charge or payment of compensation thereon and enables teachers to construct a house they would use, having built it with their own preference.

E. **"Teacher Needing Special Support"** shall mean any teacher who is physically disabled and covered under the provision of Art. 2, Sub-Art. (1) of the Federal Government Physically Disabled Persons' Right to Employment Proclamation No.568/2008 and whose status has been established by a medical board and henceforth believed by the executive committee that the extent of his disability would cause an impact on his right to benefit from equal opportunity for employment. .

F. **(Sub-municipality) or (Emerging town)** shall mean a local urban community structured under a certain lead municipality or any communal group that is found in a condition of emergence into a status of a town, wherein no municipality has not been established, in order of their priorities.

G. **"Lead Municipality"** shall mean a municipality which embraces those sub-municipalities and emerging towns found in a Woreda and is thus vested with the responsibility of coordinating and directing over their respective duties thereof.

ሸ. "አነስተኛ የከተማ አስተዳደር" ማለት በቀበሌዎች የተከፋፈለ ሆኖ ከወረዳ ተለይቶ የራሱ ውስጣዊ አስተዳደር ያለው ማናቸውም ከተማ ነው፡፡

ቀ. "መካከለኛ የከተማ አስተዳደር" ማለት በአነስተኛና በሜትሮፖሊታን የከተማ አስተዳደሮች መካከል ያለ ማናቸውም የከተማ አስተዳደር ሲሆን የዞን አስተዳደር ማዕከላትን ይጨምራል፡፡

በ. "ሜትሮፖሊታን የከተማ አስተዳደር" የሚለው ሀረግ የባህርዳር፣ የጎንደርና የደሴ ከተሞችን ይገልፃል፡፡

ተ. "ቢሮ" እና "የቢሮ ኃላፊ" ማለት እንዳግባብነቱ የክልሉ ትምህርት፣ ጤና፣ ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን፣ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ ግብርና ወይም ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮና የዚሁ ቢሮ ኃላፊ ነው፡፡

ቸ. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

2. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ማናቸውም ጉዳይ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ ከዚህ በላይ በአንቀጽ (2) ንኡስ አንቀፅ (1) ፊደል ተራ ቁጥሮች ሀ.ና ለ. ስር የተጠቀሱትን የክልሉን መምህራን፣ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

H. "Smaller City Administration" shall mean any city which has been categorized into Kebeles and acquired its own internal administration, having broken away from the Woreda thereof.

I. "Medium City Administration" shall mean any city administration which is found between small and metropolitan city administrations and include the centers of zonal administrations.

J. The term **"Metropolitan City Administration"** shall refer to those cities of Bahir Dar, Gondar and Dessie.

K. "Bureau and Bureau Head" shall be the Regional Education, Health, Urban Development, Housing and Construction or Rural Land Administration and Use, Agriculture, and Labor and Social Affairs Bureau and the head of such Bureau, as appropriate.

L. "Person" shall mean any natural or juridical person.

2. All provisions of this regulation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

3. Scope of Application

1. This regulation shall apply with regard to the region's teachers, schools and colleges specified under Art. 2 Sub-Art. (1) letter numbers A. and B. herein above.

4. አላማዎች

ደንቡ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፦

1. መምህራን የተመቻቸ የመኖሪያ አካባቢ ተፈጥሮላቸው ሙያዊ ብቃታቸውንም ሆነ ስነ-ምግባራቸውን እያሳደጉ በስራቸው ላይ በመቆየት የተማሪዎችን ውጤታማነት በቀጣይነት በማሻሻል በክልሉ ውስጥ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

2. መምህራን በተሰማሩበት የስራ መስክ ተረጋግተው በመቆየት የማስተማር ፍላጎታቸውም ሆነ ተነሳሽነታቸው እንዲጨምርና ለመማር-ማስተማሩ ሂደት የበኩላቸውን ገንቢ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማበረታታት፤

3. ለመምህርነት ሙያ ተገቢውን ክብር በመስጠት ይኸው በተማሪዎችና በህብረተ-ሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት በማሳደግ የተሻለ እውቀት ያላቸው ዜጎች ወደሙያው እንዲሳቡ ማድረግ፤

4. የትምህርት ጊዜን በአግባቡ ተጠቅሞ የመምህራንና ተማሪዎችን ስነ-ምግባር በማሻሻል በትምህርት ውጤታማነት ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ፤

5. የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ አካል ጉዳተኛ መምህራን በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀፅ (5) ስር የሰፈረውን አላማ በሚያሳካ መንገድ መደገፍ::

4. Objectives

The Regulation shall have the following objectives:

1. Following the creation of favorable living environment for teachers as well as improvement of their professional competence and ethical conduct and retain them in their career, cause the realization of quality education throughout the region by continuously enhancing the performance results of students;

2. By having them maintained in the career they have engaged themselves in, to encourage teachers so that their interest and initiation would be boosted and thereby contribute their own constructive share for the learning-teaching process per'se;

3. To cause those citizens having better knowledge to be attracted into the field by giving appropriate respect to the teaching profession and increasing the acceptance of such by students and the community;

4. To cause the bringing about of positive change with regard to the success in education by having properly used the academic duration and improving the ethical conduct of both teachers and students alike;

5. To back up those teachers with physical disabilities benefiting from special support in a way as to achieve the objective laid down under Art. 41 Sub-Art. (5) of the Constitution.

ክፍል ሁለት

ስለመብቱ አፈጻጸም

5. የእኩል መስተንግዶ መርህ

1. በክልሉ ውስጥ የገጠሩና የከተማው ነባራዊ ሁኔታዎች የተለያዩ ከመሆናቸው የተነሳ የመኖሪያ ቤትም ሆነ የዚሁ መስሪያ ቦታ አሰጣጥ ስርዓቱ የሚለያይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሁሉም አካባቢዎች ተመድበው በሚያገለግሉ መምህራን መካከል የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች አተገባበር አስመልክቶ ብሄር-ብሄረ-ሰብን፣ ሀይማኖትን፣ ማህበራዊ አመጣጥንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች መሰረት ያደረገ አንዳች አይነት ልዩነት አይደረግም፡፡ ሁሉም ያለአድልዎ የመስተናገድና በእድሉ እኩል የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡

2. በክልሉ መንግስት አማካኝነት የተሰራ መኖሪያ ቤት ያለ እንደሆነ መምህራን ይህንኑ እንዳግባብነቱ ከኪራይ ነጻ በሆነ መንገድ ወይም በተመጣጣኝ ኪራይ የማግኘት ወይም አገልግሎታቸው 2 ዓመትና ከዚያ በላይ በሆነ ጊዜ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ የሚሆን ባዶ ቦታ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ የመኖሪያ ቤትም ሆነ የባዶ ቦታ አሰጣጥ ስርዓቱ በተቻለ መጠን የተጠቃሚዎቹን ፍላጎት ያማከለ ይሆናል፡፡

PART TWO

Implementation of the Right

5. Principle of Equal Treatment

1. Due to the fact that the natural conditions of rural and urban areas are quite different throughout the Regional State, without prejudice to the prevailing disparity in the delivery system of dwelling house and land for the construction of same, no discrimination shall be made amongst teachers duly assigned to serve in all localities on the basis of nation-nationality, religion, social origin and the like matters with regard to the implementation of the provisions of this regulation. All shall be treated without discrimination and have the right to equally enjoy with the opportunity thereof;

2. Teachers shall, where there exist dwelling houses constructed by the regional government, have the right to obtain same in a manner that is free from rent or with a reasonable amount of rent, as deemed appropriate, or a vacant plot of land for the purpose of constructing dwelling house where their services have been two years and above. The delivery system of the dwelling house or vacant plot of land shall conform with the interest of individual beneficiaries, as much as possible.

3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) ስር የተደነገገው ቢኖርም መምህራኑ የደንቡ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ከመኖሪያ መንደር፣ ከኮንዶሚኒም፣ መንግስት ከሚሰጠው የኪራይ ቤት ወይም በምሪት ቦታ ከተሰሩ ቤቶች መካከል አንደኛውን ብቻ በመምረጥ ይሆናል።

6. ስለመምህራን ነጻ የመኖሪያ ቤትና ቦታ አሰጣጥ፡-

1. በንዑስ ማዘጋጃ-ቤቶች፣ በታዳጊ ከተሞችና በገጠር ቀበሌዎች ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን፡-

ሀ. ጉዳዩ በሚመለከተው ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ወይም በዙሪያ አካባቢው በክልሉ መንግስት በጀት ወይም በአካባቢው ህብረተሰብ የቁሳቁስና የጉልበት ተሳትፎ በተሰሩ የመምህራን መኖሪያ መንደሮች ውስጥ በነጻ እንዲኖሩ ይደረጋል፤

ለ. እነዚሁ የመምህራን መኖሪያ መንደሮች በዋነኛነት በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ የመማር ማስተማሩን ስራ በማያውክ ርቀት ላይ ይገነባሉ፤

ሐ. በተባለው ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ወይም በዙሪያ አካባቢው በቂ መሬት ያልተገኘ እንደሆነ አግባብ ያለው የቀበሌ አስተዳደር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተመካክሮ በሚያመቻቸው አቅራቢያ ቦታ ላይ ይገነባሉ።

3. Notwithstanding the provision of Sub-Art. (2) of this Article hereof, teachers shall be able to become beneficiaries of the regulation only by preferring one from amongst the residential village, condominium, rental house to be provided for by the government or those houses constructed on the land permitted for the purpose.

6. Delivery of Free Dwelling House and Land for Teachers

1. Teachers who happen to teach at those schools found in sub-municipalities, emerging towns and rural Kebeles:

A. shall be made to reside in the teachers' residential villages duly constructed by the Regional Government budget or through the material and labor participation of the local community in the premises of the school concerned or the surrounding area;

B. these teachers' residential villages shall be constructed mainly in the premises of the school in a distance where they do not disturb the teaching-learning activity;

C. Where adequate plot of land is not available in the premises of the said school or the surrounding area, the teachers' residential houses shall be constructed nearby in a place to be set aside by the pertinent Kebele Administration in consultation with the organs concerned thereto.

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎታቸው 2ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ መምህራን በሚሰሩበት ትምህርት ቤት15 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ ከሚገኙት ከተሞች በመረጡት በአንደኛው በራሳቸው ወጪ የግል መኖሪያ ቤት መስራት እንደሚፈልጉ ገልፀው ያመለከቱ እንደሆነ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለነባርና አዳዲስ የህብረት ስራ ማህበራት ጥር 12 ቀን 2009 ዓ.ም አሻሽሎ ባወጣው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አቅርቦትና የግንባታ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 28/2009ዓ.ም ውስጥ የተመለከተውን የማህበራት ቦታ ስፋት ልክ ሳያልፍ የጠየቁት የቤት መስሪያ ቦታ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ይኸው በኮሚቴ እየተጣራ በንዑስ ማዘጋጃ-ቤት ከተሞች ሲሆን በሊዝ መነሻ ዋጋ፣ በታዳጊ ከተሞች ሲሆን ደግሞ በአመታዊ ኪራይ ተመን ይሰጣቸዋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በ15 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ ተፈላጊውን የከተማ ቦታ ማግኘት ያልቻሉ መምህራን ቢኖሩ በአቅራቢያቸው በሚገኙ የቀበሌ ማእከላት ውስጥ የጠየቁት የቤት መስሪያ ቦታ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

2. Without prejudice to the general provision laid down under Sub-Art. (1) of this Article hereof, where teachers whose service has been two years and above notify that they preferentially desire to construct private dwelling houses on their own expense in one of the cities found within the radius of 15 kilometers from the school in which they work, they may be provided with the plot of land they have requested for the construction of house not exceeding the limit of the cooperative land size indicated under the Revised Dwelling Houses Construction Land Supply and Building Determination Directive No. 28/2017 which the Council of the Regional Government has issued on January 20 2017 for the benefit of the old and new cooperative societies. Such shall be scrutinized via a committee and be provided to them through an initial lease price, where the land is located in sub-municipalities, and through annual rental rate in the case of emerging towns.

3. Without prejudice to the provision laid down under Sub-Art. (2) of this Article hereof, should there exist teachers who have been unable to obtain the required urban land within the radius of 15 kilometers, they may be provided with the plot of land they have requested at the Kebele center located in their surroundings.

4. መምህራን በሚሰሩበት ወረዳ ውስጥ ካሉት ከተሞች መካከል ራሳቸው በመረጡት ከተማ ውስጥ የመኖሪያ ቤት ለመስራት የፈለጉ እንደሆነ መመሪያ ቁጥር 28/2009 ዓ.ም በሚፈቅደው መሰረት እንደማንኛውም ዜጋ 14ና ከዚያ በላይ እየሆኑ በማህበር ተደራጅተውና ከቤት መስሪያ ዋጋው 20 ከመቶ የሚሆነውን ገንዘብ መቆጠባቸውን አረጋግጠው ቦታውን ሊያገኙ ይችላሉ።

5. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ ቢኖርም ቀደም ሲል በማህበር ተደራጅተው የቤት መስሪያ ቦታ የተረከቡ መምህራን በዚሁ በተረከቡት ቦታ ላይ የአካባቢው አስተዳደር ያወጣውን ደረጃ የጠበቁ መኖሪያ ቤቶችን በራሳቸው ወጪ ሊገነቡ ይችላሉ።

6. በከተማው ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ከሚዘጋጀው ቦታ ውሥጥ ከ20-30 ከመቶ የሚሆነው ለመምህራን ቅድሚያ ተሰጥቶ ይመደባል።

7. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሰረት መምህራንን ተጠቃሚ ለማድረግ ሲባል የካሳ ክፍያ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የክልሉ መንግስት ለተፈናቃዮቹ በህግ አግባብ ተገቢውን ካሳ በቅድሚያ በመክፈል ወይም ትክ ቦታ በመስጠት የቤት መስሪያ ስፍራውን ከሶስተኛ ወገን ነጻ ያደርጋል።

4. Where teachers desire to construct a dwelling house in the town they have preferred among the cities existing in the Woreda wherein they work, they may, having been organized in cooperatives of 14 in number and ascertained that they have managed to save the money to the amount of 20% of the total price for the construction of the house, obtain such land in accordance with the Directive No. 28/2017.

5. Notwithstanding the provision of Sub-Art. (4) of this Article hereof, teachers who already had been organized in cooperatives and received land for the construction of houses may build same having maintained the standard set by the local administration on their expense at such land they have acquired thereof.

6. 20 through 30% of the land to be prepared for the construction of dwelling houses in the city shall be allotted for teachers, having been given priority thereof.

7. Where payment of compensation is a necessity to benefit teachers in accordance with the provisions of this regulation, the regional government shall make the land for housing construction free from third party by, in advance, disbursing the appropriate compensation in line with the law to the displaced persons or providing substitute plots of land for them.

7. በአነስተኛ ከተማ አስተዳደሮች ስር በተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ስለሚያስተምሩ መምህራን፡-

1. የራሳቸው አስተዳደር ባላቸው አነስተኛ ከተሞች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን በትምህርት ቤቶቻቸው አካባቢ በክልሉ መንግስት በጀትና በህዝብ ተሳትፎ ደረጃ በደረጃ በሚሰሩ የመኖሪያ መንደሮች በነፃ እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በመስኩ ያበረከቱት አገልግሎት 2 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ መምህራን በራሳቸው ወጪ የግል መኖሪያ ቤት መስራት የፈለጉ እንደሆነ መመሪያ ቁጥር 28/2009 ዓ.ም በሚፈቅደው መሰረት ቁጥራቸው 14ና ከዚያ በላይ እየሆኑ በማህበር ተደራጅተው ቦታ ከጠየቁና ከቤቱ መስሪያ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ 20 ከመቶ የሚሆነውን ስለመቆጠባቸው ካረጋገጡ ቦታው በሊዝ መነሻ ዋጋ ይሰጣቸዋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተመለከተው ቢኖርም ጥያቄ አቅራቢ መምህራኑ ቁጥራቸው ከ14 በታች በሆነ ጊዜ በተናጠልም ቢሆን በሊዝ መነሻ ዋጋ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የማግኘት መብታቸው ይጠበቅላቸዋል፡፡

7. Teachers Teaching in Schools Established under Smaller City Administrations

1. Teachers who happen to teach in smaller cities having their own administrations shall be made to reside freely in the residential villages to be constructed, step by step, in the surrounding area of their schools by the regional government's budget and the participation of the public.

2. Without prejudice to the provision laid down under Sub-Art. (1) of this Article hereof, where those teachers, whose service contributed in the field has lasted two years and above, so desire to construct private dwelling houses on their own expense and thereby request for land by having organized themselves in cooperatives numbering 14 and above as well as ascertained that they have managed to save 20% of the total price of the housing construction as permitted by the Directive No. 28/2017, such land shall be provided for them at the initial lease price.

3. Notwithstanding the provision laid down under Sub-Art. (2) of this Article hereof, where the number of those teachers submitting the request is below 14, their right to obtain land for the construction of dwelling houses at the initial lease price shall be respected even on an individual status.

4. ከዚህ በላይ በአንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፆች (5)፣ (6)ና (7) ስር በንኡስ ማዘጋጃ-ቤቶች፣ ታዳጊ ከተሞችና የገጠር ቀበሌዎች ውሥጥ በተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራንን በተመለከተ የሰፈሩት ድንጋጌዎች በአነስተኛ የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ለሚያስተምሩ አቻዎቻቸውም በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

8. በመካከለኛ የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ባሉ ትምህርት ቤቶች ስለሚያስተምሩ መምህራን፡-

1. በመካከለኛ የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በትምህርት ቤቶቻቸው አካባቢ በክልሉ መንግስት በጀትና በህዝብ ትብብር ደረጃ በደረጃ በሚገነቡ የመምህራን መኖሪያ መንደሮች ውስጥ ያሉ ቤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ተከራይተው እንዲኖሩ ይደረጋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም በመስኩ ያበረከቱት አገልግሎት 2 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ መምህራን በራሳቸው ወጪ የግል መኖሪያ ቤት መስራትን የመረጡ እንደሆነ መመሪያ ቁጥር 28/2009ዓ.ም በሚፈቅደው መሰረት ቁጥራቸው 14ና ከዚያ በላይ እየሆኑ በማህበር ተደራጅተውና ከቤቱ መስሪያ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ 20 ከመቶ የሚሆነውን ስለመቆጠባቸው አረጋግጠው የጠየቁት ቦታ በከተማው የሊዝ መነሻ ዋጋ ሊሰጣቸው ይችላል።

4. The provisions laid down under Sub-Arts. (5), (6) and (7) of Art. 6 herein above with regard to the teachers teaching in schools set up under sub-municipalities, emerging towns and rural Kebeles shall Mutatis mutandis apply to their counterparts teaching in smaller city administrations.

8. Teachers Teaching at Schools Located in the Medium City Administrations

1. Teachers teaching at schools found in the Medium City Administrations shall be made to reside in those houses existing in the teachers' residential villages to be constructed, step by step, by the regional government's budget in collaboration with the public in the surrounding area of their schools, having accessed them with a reasonable amount of rent.

2. Notwithstanding the provision laid down under Sub-Art. (1) of this Article hereof, where those teachers, whose service contributed in the field has lasted two years and above, prefer to construct private dwelling houses on their own expense and thereby request land by having organized themselves in cooperatives numbering 14 and above in accordance with the Directive No. 28/2017 as well as ascertained that they have managed to save 20% of the total price of the housing construction, such land which they have requested shall be provided to them at the city's initial lease price.

3. ከዚህ በላይ የሰፈረው ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም የጥያቄ አቅራቢዎቹ ቁጥር ከ14 በታች በሆነ ጊዜ መምህራኑ በተናጠልም ቢሆን የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሊዝ መነሻ ዋጋ ሊሰጣቸው ይችላል።

4. ይህ የማይቻልበት ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ የከተማ አስተዳደሩ ለከተማው ነዋሪዎች ከሚገነባቸውና ለክልሉ መንግስት ሰራተኞች ከሚሰጣቸው አፓርተማዎች ወይም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ 20 ከመቶ በሚሆነው ድርሻ እኩል የሚጠቀሙ መሆናቸው ሳይቀር መምህራን 10 ከመቶ ተጨማሪ እድል ተሰጥቷቸው እርስ በርሳቸው ለብቻ ይወዳደራሉ።

5. ከዚህ በላይ በአንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፆች (5)፣ (6)ና (7) ስር በንኡስ ማዘጋጃ-ቤቶች፣ ታዳጊ ከተሞችና የገጠር ቀበሌዎች ውሥጥ በተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራንን በተመለከተ የሰፈሩት ድንጋጌዎች በመካከለኛ የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ለሚያስተምሩ አቻዎቻቸውም በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

9. በሜትሮፖሊታን ከተሞች ስለሚያስተምሩ መምህራን፡-

1. በሜትሮፖሊታን ከተሞች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን የክልሉን መንግስት አቅም ባገናዘበ ሁኔታ የጋራ መኖሪያ መንደር ደረጃ በደረጃ ከተገነባ በኋላ ቤቱ በተመጣጣኝ ኪራይ እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

3. Notwithstanding the provision of Sub-Art. (2) laid down herein above, where the number of teachers submitting the request is below 14, they may be provided with the land for the construction of dwelling houses against the city's initial lease price, even on an individual basis.

4. Where such an impossible condition has been encountered, teachers shall, without regard to the fact that they equally benefit from the 20% share out of the apartments or condominiums to be constructed by the city administration for the urban dwellers and allocated for the regional civil servants, solely compete amongst themselves, having been given ten percent additional opportunity.

5. The provisions laid down under Sub-Arts. (5), (6) and (7) of Art. 6 herein above with regard to those teachers teaching at schools set up under sub-municipalities, emerging towns and rural Kebeles shall mutatis mutandis apply to their counter-parts teaching in the medium city administrations.

9. Teachers Teaching in the Metropolitan Cities

1. Following the construction, step by step, of condominiums by taking the capacity of the regional government into consideration, the houses therein shall be provided for teachers who happen to teach at the schools found in the metropolitan cities with a reasonable amount of rent.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በመስኩ ያበረከቱት አገልግሎት 2 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ መምህራን በራሳቸው ወጪ የግል መኖሪያ ቤት መስራት የፈለጉ እንደሆነ መመሪያ ቁጥር 28/2009 ዓ.ም በሚፈቅደው መሰረት ቁጥራቸው 14ና ከዚያ በላይ እየሆኑ በማህበር ተደራጅተው ከጠየቁና ከቤቱ መስሪያ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ 10 ከመቶ የሚሆነውን ስለመቆጠባቸው ካረጋገጡ ቦታው በከተማው ሊዝ መነሻ ዋጋ ይሰጣቸዋል።

2. Without prejudice to the provision laid down under Sub-Art. (1) of this Article hereof, where those teachers, whose service contributed in the field has lasted two years and above, so desire to construct private dwelling houses on their own expense and thereby request for land by having organized themselves in cooperatives numbering 14 and above in accordance with the Directive No. 28/2017 as well as ascertain that they have managed to save 10% of the total price of the housing construction, such land shall be provided to them against the city's initial lease price.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተመለከተው ቢኖርም ጥያቄ አቅራቢ መምህራኑ ቁጥራቸው ከ14 በታች በሆነ ጊዜ በተናጠልም ቢሆን በከተማው ሊዝ መነሻ ዋጋ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የማግኘት መብታቸው ይጠበቅላቸዋል።

3. Notwithstanding the provision indicated under Sub-Art. (2) of this Article hereof, where the number of teachers submitting the request is below 14, their right to obtain land for the constructionn of dwelling houses against the city's initial lease price shall be respected, even on an individual status.

4. በሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች ስር በሚጠቃለሉ የገጠር አካባቢዎች በተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን ጥያቄ አግባብ ያላቸውን የዚህን ደንብ አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ለማስተማር በተመደቡባቸው የገጠር ቀበሌ ማዕከላት በኩል ይስተናገዳል።

4. The request of those teachers serving at the schools set up in the rural areas embraced in the metropolitan city administrations shall be addressed on the part of the rural Kebele centers, wherein they have been assigned to teach, in accordance with the pertinent provisions of Art. 6 of this Regulation hereof.

5. ከዚህ በላይ በአንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፆች (5)፣ (6)ና (7) ስር በንኡስ ማዘጋጃ-ቤቶች፣ ታዳጊ ከተሞችና የገጠር ቀበሌዎች ውሥጥ በተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራንን በተመለከተ የሰፈሩት ድንጋጌዎች አግባብነታቸው እየታየ በሜትሮፖሊታን ከተሞች ውስጥ ለሚያስተምሩ አቻዎቻቸውም በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ክፍል ሶስት

የተጠቃሚ መምህራን መብቶችና ግዴታዎች

10. የተጠቃሚ መምህራን መብቶች

1. በክልሉ ውስጥ በየትኛውም ስፍራ (ውርስን ሳይጨምር) በራሳቸውም ሆነ በትዳር አጋሮቻቸው ስም አስቀድሞ የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም ቦታ የሌላቸው ስለመሆኑ በክልሉ ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮና የተዋረድ አደረጃጀቶቹ አማካኝነት ተጣርቶ የተረጋገጠላቸው መምህራን ከዚህ በታች የተመለከቱት መብቶች አሏቸው፡-

ሀ. የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የመጠየቅና የማግኘት፤

5. The provisions laid down under Sub-Arts. (5), (6) and (7) of Art. 6 herein above shall, with regard to the teachers serving at the schools set up under sub-municipalities, emerging towns and rural Kebeles, shall, mutatis mutandis, apply to their counterparts teaching in metropolitan city administrations, having due regard to their appropriateness.

PART THREE

RIGHTS AND OBLIGATIONS OF TEACHERS ENTITLED FOR THE BENEFIT

10. Rights of Teachers Entitled for the Benefit

1. Teachers, about whom it has been established on the part of the Regional Urban Development, Housing and Construction Bureau and its hierarchical structures, that they have not, except through inheritance, acquired a dwelling house or plot of land previously registered in their own name or that of their spouse at any place throughout the Regional State, shall enjoy the rights specified here-below:

A. To request for and obtain a plot of land for the construction of a dwelling house;

ለ. አቅምን ባገናዘበ ሁኔታ በክልሉ መንግስት ወጪ ከተገነቡት ወይም ወደፊት ከሚገነቡት አፓርተማዎች ውስጥ ለመምህራን ተለይቶ በተሰጠው እድል ተወዳዳሪና ተጠቃሚ የመሆን፤

ሐ. መኖሪያ ቤትም ሆነ ቦታ የሌላቸው ባለትዳር መምህራን የጋራ መኖሪያ ቤት ወይም ይህንኑ ለመስራት የሚያገለግል ቦታ ለማግኘት ይቻላቸው ዘንድ በተናጠል የመወዳደርና ሁለቱም ያገኙ እንደሆነ ደግሞ በመረጡት በአንደኛው እድል የመጠቀም ::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሐ. ድንጋጌ ስር በተመለከተው አኳኋን ባልና ሚስት የሆኑ መምህራን በየራሳቸው እጣ ተወዳዳሪዎች መሆናቸውን ተከትሎ ባገኙት ወይም በመረጡት መኖሪያ ቤት በመጠቀም ላይ እያሉ ጋብቻቸው በፍች የተቋረጠና የተለያዩ እንደሆነ ከሁለቱ ተጋቢዎች መካከል ቤቱን በብቸኝነት አስቀርቶ በመጠቀም ረገድ ለሴቷ የቀደምትነት መብት ይጠበቅላታል፡፡ ሆኖም ሴቷ መምጎርት ሆና ካልተገኘች ጋብቻው ከተቋረጠበት እለት አንስቶ በሚቆጠር የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የያዘችውን ቤት መልቀቅ ይኖርባታል፡፡

B. To be a competitor for and beneficiary of the opportunity specifically granted for teachers with a view to obtaining one from among the apartments constructed or to be constructed in future with the expense of the Regional Government taking into consideration the capacity thereof;

C. With regard to those spousal teachers having neither a dwelling house or plot of land, to compete on an individual basis with a view to acquiring a condominium house or a plot of land enabling them to construct same and to take either of the two lots on their own preference, in case both of them have manage to win the lot.

2. Where the marriage of spousal teachers has been dissolved and are thus separated by divorce while using a dwelling house acquired or preferred by both of them following the fact that they have competed in their individual draws in a manner indicated under Sub-Art. (1) C. of this Article hereof a preemptory right shall be given to the female with regard to keeping and solely utilizing the house from the two members of the couple; provided, however, that, if the wife is not found to be a teacher, she ought to vacate such house within the period of six months starting from the day on which their marriage has been terminated.

3. ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀፅ (2) ስር የተደነገገው ቢኖርም ከቅን ልቦና ውጭ የተከናወነ ማናቸውም የጋብቻ ፍች ከተጋቢዎች መካከል ማንኛቸውንም ቢሆን የሁለቱም ቤቶች ወይም ቦታዎች እድል ተጠቃሚ ሊያደርግ አይችልም።

4. የራሳቸው ቤት ወይም ቦታ የሌላቸውና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መምህራን አገልግሎቱን በማግኘት ረገድ ከሁሉም እጩ ተወዳዳሪዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

11. የተጠቃሚ መምህራን ግዴታዎች

1. ማንኛውም መምህር ከሙያው በጡረታ ሲገለል ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ስራውን ሲለቅ ይኖርበት የነበረውን የመንግስት ቤት በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በመልቀቅ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል የማስረከብ ግዴታ አለበት።

2. ማንኛውም መምህር በመምህራን መኖሪያ መንደር ውስጥ በመኖር ላይ ሳለ ከዚህ አለም በሞት የተለየና የትዳር አጋሩ መምህር/ት ካልሆነ/ች ቤቱን በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ አስረክቦ/ባ ይወጣል/ለች፤ ሆኖም ግራ ቀኙ መምህራን ሆነው በፍች የተለያዩ እንደሆነ በቤቱ የመቆየት ቅድሚያ ለሴቷ ተሰጥቶ ወንዱ እንዲወጣ ይደረጋል።

3. Notwithstanding the provision specified under Sub-Art. (2) herein above, no marital divorce carried out in a way other than good faith may make anyone of the ex-couple the undue beneficiary of any opportunity of gaining houses or plots of land either.

4. Teachers who do not have their own house or plot of land and are in need of special support shall be given priority over all other candidate competitors with regard to acquisition of the service thereof.

11. Obligations of Teachers Entitled for the Benefit

1. Where any teacher has retired from his profession or resigned from job for any reason shall have the obligation to leave the government house in which he was dwelling within the period of six months and hand it over to the organ concerned.

2. Where any teacher has passed away as he was dwelling in the teachers' residential village and his/her spouse is not a teacher, he/she shall leave the house and hand it over within the period of six months; provided, however, that, where both of them happen to be teachers and have been separated due to divorce, the priority to stay therein shall be given to the woman with the man to be made to leave there-from.

3. በመምህራን የጋራ መኖሪያ መንደር ተጠቃሚ ለመሆን የሚያመለክት ማንኛውም መምህር ለስራ በተመደበበት ከተማ ውስጥ በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ስም የተመዘገበ የግል መኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ስለመሆኑ ጉዳዩን ለሚያጣራው አካል ትክክለኛ መረጃ የመስጠትና ውል የመግባት ግዴታ አለበት።

4. ማንኛውም መምህር የክልሉ መንግስት ለመምህራን ጥቅም ባመቻቸው የጋራ መኖሪያ መንደር ሲኖር በዚህ ደንብ መሰረት በሃላፊነት ተረክቦ የሚገለገልበትን ቤት በንፅህና የመያዝ፣ በግል የሚፈለጉበትን እንደ ውሀ፣ መብራት፣ ስልክ፣ ኢንተርኔትና የመሳሰሉትን የአገልግሎት ክፍያዎች በወቅቱ የመፈፀምና የመንደሩን መተዳደሪያ ደንብ የማክበር ግዴታዎች ይኖሩበታል።

12. በመምህራን የጋራ መኖሪያ መንደር ስለሚገነቡ ቤቶች ድልድል፡-

1. መምህራንን በዚህ ደንብ መሰረት ተጠቃሚ የሚያደርገው የጋራ መኖሪያ መንደር ግንባታ እንደተጠናቀቀ ድልድሉ የሚከናወነው በመምህርነት የተሰጠን አገልግሎትና የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚነትን መሰረት በማድረግ ሆኖ፡-

3. Any teacher applying to be the beneficiary of the teachers' residential village shall have the obligation to provide accurate information to the organ investigating the matter that he does not have a private dwelling house or a plot of land for the construction thereof registered in his own name or that of his spouse in the city in which he has been assigned for duty and to enter into contract thereof.

4. Where any teacher dwells at the common residential village facilitated by the regional government for the benefit of teachers, he shall have the obligations to keep the house which he has responsibly received for utilization clean and timely disburse the service charges of water, electricity, telephone, internet and the like as well as observe the bylaw of such village.

12. Distribution of Houses to Be Constructed at the Teachers' Common Residential Village

1. No later than the completion of the construction of the common residential village for the benefit of teachers in pursuance of this regulation, the distribution shall be carried out on the basis of the service rendered as a teacher and the beneficial status having to do with special support:

ሀ. በሜትሮፖሊታን ከተሞች ውስጥ ሲሆን በሙያው ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በአገልግሎት ላይ የቆዩበት ጊዜና የየቤተሰቦቻቸው ብዛት እየታየ ባለአንድ፣ ባለሁለትና ባለሶስት ምኝታ ክፍል/ሎች ቤት በተመጣጣኝ ኪራይ ይሰጣቸዋል፤

A. While in the metropolitan cities, they shall be provided with a house having one, two or three bedrooms against a reasonable amount of rent in consideration of the duration in which they have served in the profession as of the time of their recruitment and the number of their family members;

ለ. በመካከለኛና በአነስተኛ የከተማ አስተዳደሮች፣ በመሪና በንኡስ ማዘጋጃ-ቤቶች፣ በታዳጊ ከተሞችና በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን እንደየትምህርት ቤቱ ተጨባጭ ሁኔታ በቅጥር ግቢው ወይም በሙሪያ አካባቢው የጋራ መኖሪያ መንደር እየተገነባ በነፃ እንዲደርሳቸው ይደረጋል::

B. those teachers who happen to teach at the schools found in the medium and smaller city administrations, lead and sub-municipalities, emerging towns and the rural Kebele centers shall be made to have free access to the communal residential village to be constructed in the premises thereof or the surrounding areas, depending on the concrete situation of each and every school concerned.

2. አካል ጉዳተኞችን አስመልክቶ በሀገሪቱ የወጡ ሕግጋት እንደተጠበቁ ሆነው በክልሉ ውስጥ የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ መንደሮችና በውስጣቸው የሚካተቱ ቤቶች ዜጎች ያሉባቸውን አካላዊ ችግሮች ያገናዘቡ ሆነው እንዲታነፁ ከማድረግ በተጨማሪ ግንባታቸው በተጠናቀቀ ቤቶች ድልድል ረገድም እነዚሁ ወገኖች የቀደምትነት መብት ይጠበቅላቸዋል::

2. Without prejudice to the laws issued in the country with regard to ppersons with disabilities, in addition to causing the communal residential villages to be constructed throughout the Regional State and houses therein to be built by having taken the physical constraints of citizens into consideration, as far as the distribution of such houses, whose construction has been completed, is concerned, the preemptory right of such persons shall be protected thereof.

3. ሴት መምህራን ከወንዶች አቻዎቻቸው የቀዳሚነት መብት አላቸው::

4. አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሴት መምህራን በጾታና በአካል ጉዳት ምክንያት ያለባቸውን ተዳራራቢ ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባት ከሁሉም እጩዎች የቀዳሚነት መብት የሚጠበቅላቸው ሲሆን ለውድድር የቀረበው መኖሪያ ቤት አንድ ብቻ ሆኖ ካአንድ በላይ የሆኑ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡበት ጊዜ የእድሉ አሸናፊዎች በእጣ እንዲለዩ ይደረጋል::

ክፍል አራት

ስለደንቡ አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና ተግባር

13. ስለ ቢሮዎች በጠቅላላው

ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ ግንባር-ቀደም ሆነው የተሰየሙ የክልሉ ቢሮዎች የሚከተሉት አበይት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሯቸዋል:-

1. በደንቡ አተገባበር የሚሳተፉ ኮሚቴዎች፣ ባለሙያዎችና ተጠቃሚዎች በቂ ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ያደርጋሉ፣ ተፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ፤

2. እንደየስራ ዘርፎቻቸው የደንቡን ሙሉ ተፈጻሚነት በቅርበት ይከታተላሉ፣ ይቆጣጠራሉ::

3. Female teachers shall have a prior right to their male colleagues.

4. The prior right of female teachers with physical disabilities shall, taking their multiple problems attributable to gender and physical disability into account, be protected over all other candidates, and where the house put for acquisition through competition happens to be only one and more than one competitors have appeared to so claim it, winners of the opportunity shall be identified by casting a lot.

PART FOUR

ORGANIZATION AND DUTIES OF EXECUTIVE ORGANS OF THE REGULATION

13. The Bureaus in General

The Regional Bureaus designated as such on the forefront with regard to the implementation of this regulation shall have the following major duties and responsibilities:

1. cause the creation of adequate awareness for the committees, experts and beneficiaries participating in the implementation of the Regulation and provide them the necessary support thereto;

2. Closely follow up and supervise over the full implementation of the regulation depending on the duties pertaining to their respective sectors.

14. ስለርዕሰ-መስተዳድሩና በተዋረድ ስለሚገኙ የየዞኑ ዋና አስተዳዳሪዎች ተግባርና ሃላፊነት

የክልሉ ርእሰ-መስተዳድርና የየዞኑ ዋና አስተዳዳሪዎች በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት አበይት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡-

1. ይህንን ደንብ በክልል ደረጃ ለማስፈጸም አስፈላጊው በጀት በወቅቱ እንዲመደብ ያደርጋሉ፣ የበላይ አመራር ይሰጣሉ፣ ይቆጣጠራሉ፤

2. በመምህራን የጋራ መኖሪያ መንደሮች ግንባታ ማህበረሰቡ የበኩሉን ድርሻ ይወጣ ዘንድ አስፈላጊውን የማስተባበር ስራ ያከናውናሉ።

15. የትምህርት ቢሮና የተዋረድ አካላቱ ተግባርና ሃላፊነት

የክልሉ ትምህርት ቢሮ ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. አላማዎቹን ለማህበረ-ሰቡ በስፋት ያስተዋውቃል፣ አግባብነት ላላቸው አካላት አስፈላጊ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤

2. የደንቡን ገቢራዊነት አስመልክቶ ከዞን እስከወረዳ ላሉና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

14. Duties and Responsibilities of the Head of Government and the Hierarchically found Zonal Chief Administrators

The Head of the Regional Government and Zonal Chief Administrators shall, pursuant to this regulation, have the following duties and responsibilities:

1. Cause the setting aside, on time, of the required budget with a view to implementing this Regulation at the Regional level, render superior leadership and supervise over thereof;

2. Carry out the necessary coordinating activity so that the community would discharge its own share with regard to the construction of the teachers' communal residential village.

15. Duties and Responsibilities of the Education Bureau and Its Hierarchical Organs

The Education Bureau shall, with regard to the implementation of this regulation, have the following specific duties and responsibilities:

1. Widely promote its objectives to the community and provide the necessary trainings to the pertinent bodies;

2. Closely follow up and thereby render support for those organs existing from The Zone through Woreda and concerned with regard to the implementation of the Regulation;

3. እንዳስፈላጊነቱ በክልሉ መስተዳድር ውሳኔ የጋራ መኖሪያ መንደሮቹን ከመንግስት በሚመደብ በጀት አሰርቶ ለተጠቃሚ መምህራን ያስረክባል፤

4. በስራ ላይ እያሉ የራሳቸው መኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ ያላቸውንና የሌላቸውን መምህራን ከየደረጃው አካላት ጋር በመተባበር ያጣራል፣ ይለያል፣ መረጃዎችን ይይዛል፤

5. መልካም ተሞክሮዎችን በማሰባሰብ በየደረጃው ለተቋቋሙ የመምህራን መኖሪያ ቤት ልማት ኮሚቴዎች ያሰራጫል፤

6. በየደረጃው የሚገኙ የመምህራን ማህበራትና ሌሎች ባለድርሻዎች የደንቡን አፈጻጸም በቅርብ እንዲከታተሉና እንዲደግፉ ያበረታታል፤

7. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጥናት ላይ የተመሰረቱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤

8. የተዋረድ አወቃቀሮቹ በስራቸው የሚገኙ የተጠቃሚ መምህራንን መረጃዎች በሚገባ አደራጅተው የመያዝና የመጠበቅ ግዴታዎቻቸውን ይወጡ ዘንድ አቅማቸውን ይገነባል።

3. Cause the construction of the communal residential villages with the budget to be allocated by the government and hand same over to the teachers entitled for the benefit , upon the decision of the regional government, as deemed necessary;

4. Verify and identify teachers possessing their own dwelling houses or land and otherwise in collaboration with the hierarchically-structured bodies and thereby maintain records of the data;

5. Collect and disseminate good practices to the teachers' housing development committees established at all levels;

6. Encourage teachers' associations found at all levels and other stakeholders so that they would closely follow up and support the implementation of the Regulation;

7. Where it is found necessary, submit amendment proposals based on a study to the council of the regional government and cause same to be determined thereof;

8. Build the capacity of its subordinate structures so that they would discharge their obligations to organize, handle and maintain the data pertaining to the teachers entitled for the benefit thereof.

16. በተዛማጅ ድንጋጌዎች ስለመስራት

ከዚህ በላይ በአንቀፅ 15 ንኡስ አንቀፆች (4)፣ (7)ና (8) ስር የክልሉን ትምህርት ቢሮ ስልጣንና ተግባራት በተመለከተ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ከየሙያ ዘርፉ አሰልጣኞቻቸውና ተቋሞቻቸው ጋር በተያያዘ የክልሉን ግብርና፣ ጤና ጥበቃ፣ ቴክኒክና ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማትም ሆነ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች በሚመለከት አግባብነታቸው እየታየ በተመሳሳይ ይሰራባቸዋል።

17. የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮና የተዋረድ አካላቱ ተግባርና ሃላፊነት

የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ይህንን ደንብ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. ለደንቡ ሙሉ ተፈፃሚነት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው በጀት በወቅቱ እንዲመደብ ያደርጋል፣ ገንዘቡን ያስተዳድራል፤

2. ለመምህራን የጋራ መኖሪያ መንደሮቹ ግንባታ ከማህበረሰቡ በኩል ሊገኝ የሚገባው ገቢ በክልሉ የፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት በወቅቱ ሊሰበሰብ የሚችልበትን የአሰራር ስልት ይዘረጋል፤

16. Working with Related Provisions

The provisions laid down under Sub-Arts. (4), (7) and (8) of Art. 15 herein above regarding the powers and duties of the Regional Education Bureau shall mutatis mutandis apply to the Regional Agriculture, Health, Technical and Vocational and Enterprises Development as well as Labor and Social Affairs Bureaus in connection with their trainers and facilities of each and every professional stream, having due consideration to their appropriateness.

17. Duties and Responsibilities of the Regional Finance and Economic Cooperation Bureau and Its Hierarchically-Structured Organs

The Regional Finance and Economic Cooperation Bureau shall, with regard to the implementation of this regulation, have the following specific duties and responsibilities:

1. Cause the setting aside of the budget necessary for the full implementation of the regulation on time and administer the funds thereof;

2. put into place a working mechanism through which the revenue subject to be derived from across the community for the construction of the teachers' communal residential villages might be collected on time in accordance with the financial laws and regulation of the Regional State;

3. በአቢይ ኮሚቴው አማካኝነት ጥያቄ ሲቀርብለት ለስራው የሚያስፈልጉት የፋብሪካ ምርቶችና ሌሎች ግብአቶች በህግ አግባብ ተገዝተው እንዲቀርቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

18. የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ ተግባርና ሃላፊነት

የክልሉ ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. ከደንቡ አተገባበር ጋር በተያያዘ በየትኛውም ጊዜ የሚቀርቡትን የተለያዩ የቦታ ጥያቄዎች በሚገባ ለማስተናገድ ያመች ዘንድ አግባብነት ያላቸውን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በማድረግ ለልማት ተነሺዎች ተገቢው ካሳ በቅድሚያ እንዲከፈል ወይም ትክ ቦታ እንዲሰጥ ከሶስተኛ ወገን ነጻ የሆነ በቂ መሬት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

2. የመሬትና የግንባታ ፈቃድ ጥያቄዎች ሲቀርቡለት በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ምላሾችን ይሰጣል፣ ግንባታውን በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

3. Where a request has been submitted to it on the part of the principal committee, facilitate conditions in which the manufactured products and other inputs required for the duty are procured and supplied, in accordance with law.

18. Duties and Responsibilities of the Urban Development, Housing and Construction Bureau

The Regional Urban Development, Housing and Construction Bureau shall, with regard to the implementation of this regulation, have the following specific duties and responsibilities:

1. Cause the preparation and provision of sufficient land which is free from third party so that the appropriate compensation be disbursed in advance or a substitute plot of land be provided for the persons displaced as a result of development on the basis of the appropriate laws, regulations and directives with a view to enabling it to duly entertain the various land requests brought about at any time in connection with the implementation of this regulation;

2. Where requests for land and construction license are submitted to it, provide responses pursuant to the powers vested in it as well as closely follow up and supervise such construction;

3. ከመሰረተ-ልማት አገልግሎቶች አቅራቢ ተቋማት ጋር በመተባበር ለግንባታ የሚያስፈልጉት ግብዓቶች በወቅቱ እንዲሟሉ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፤

4. አስፈላጊ የሊዝና አመታዊ የከተማ ቦታ ኪራይ ክፍያዎች እንዲሰበሰቡ በትጋት ይሰራል፤

5. ውሰታ በተገባላቸው መሰረት ያልተከናወኑ ግንባታዎችን በሚመለከት አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

6. በየደረጃው ያሉ መዋቅሮቹ የተጠቃሚ መምህራንን መሬት-ነክ መረጃዎች በሚገባ ለመያዝና ለመጠበቅ ያለባቸውን ሃላፊነት ይወጡ ዘንድ አቅማቸውን ይገነባል፤

7. የዚህን ድንጋጌዎች በሚገባ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ያወጣል።

19. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ተግባርና ሃላፊነት

የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፦

3. Properly strive so that inputs necessary for t construction are timely furnished collaboration with those institutions charge with the infrastructural services;

4. Work diligently for the collection of the necessary charges of lease and annual urban land rentals;

5. Take the necessary rectification measures with regard to the constructions not accomplished pursuant to the contract that has been concluded thereof;

6. Build the capacity of its hierarchically-structured organs at all levels so that they would discharge their responsibility to properly handle and maintain the land-related information of teachers entitled for the benefit;

7. Issue detailed directives necessary for the proper implementation of the provisions of this regulation.

19. Duties and Responsibilities of the Rural Land Administration and Use Bureau

The Regional Rural Land Administration and Use Bureau shall, with regard to the implementation of this regulation, have the following specific duties and responsibilities:

1. አግባብ ባለው አካል በኩል የመሬት ጥያቄ የቀረበለት እንደሆነ ማዘጋጃ-ቤቶች ወይም የቀበሌ አስተዳደሮች ከሶስተኛ ወገን ይዞታ ነጻ የሆነ መሬት ማቅረብ በማይችሉበት ወቅት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተገቢውን የካሳ ስሌት ሰርቶ ይኸው ለባለመብቶች በቅድሚያ እንዲከፈል ወይም ትክ ቦታ እንዲመቻች ካደረገ በኋላ ተፈላጊውን መሬት በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች ያቀርባል፤

2. እንዳስፈላጊነቱ በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ ባለይዞታዎችን በጋራ የማቋቋም ስራዎችን ያከናውናል፤

3. ምንም አይነት የከተማ ቦታ አቅርቦት አማራጭ በሌለባቸው የገጠር አካባቢዎች የመምህራን የጋራ መኖሪያ መንደር የሚገነባበትን መሬት አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ያስረክባል፤

4. አዲስ የሚመሰረቱ የገጠር መምህራን መንደሮችን አግባብ ካላቸው የገጠር ቀበሌ ማእከላት ጋር ያስተሳስራል፣ ለቤቶቹ ተገቢውን ሳይት ፕላን ይሰራል፤

5. መምህራን በገጠር ቀበሌ ማእከላት የምሪት ቦታ ጥያቄ ሲያቀርቡ መሬቱን በህግ አግባብ ከሶስተኛ ወገኖች ይዞታ ነጻ አድርጎ ወቅታዊ ምላሾችን ይሰጣል።

1. Where a request for a plot of land has been submitted to it by the appropriate organ, prepare and provide such a required plot to the beneficiaries at a time when municipalities or Kebele administrations are unable to avail same free from a third parties' possession after having completed the appropriate amount of compensation in collaboration with the organs concerned and thereby cause same to be paid for those rightful possessors or facilitated the provision of a substitute plot thereof;

2. Carry out joint activities to rehabilitate those possessors displaced due to development, as deemed necessary;

3. Prepare and hand over a plot of land for the construction of the teachers' communal residential village at the rural Kebeles lacking any alternative for the provision of urban land;

4. Interconnect the rural teachers' residential villages to be newly established with the relevant rural Kebele centers and formulate a site plan for the houses therein;

5. Where teachers submit a request for land through a permit system in the rural Kebele centers, render timely response by making the land free of third party possession in accordance with law.

ክፍል አምስት

ደንቡን ለማስፈፀም በተለያዩ ደረጃዎች ስለተቋቋሙ ኮሚቴዎች

20. ስለኮሚቴዎች አይነትና የአባሎቻቸው ጥንቅር

1. በክልል ደረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አባላት የተካተቱበት አቢይ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡-

ሀ. ምክትል ርእሰ-መስተዳድሩ ---- ሰብሳቢ ፡-

ለ. የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ------- አባል፣

ሐ. የቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል፣

መ. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል፣

ሠ. የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ ---------- አባልና ጸሀፊ፣

ረ. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ሀላፊ ---------- አባል፣

ሰ. የግብርና ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል፣

ሸ. የጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል፣

PART FIVE

COMMITTEES ESTABLISHED AT VARIOUS LEVELS IN VIEW OF IMPLEMENTING THE REGULATION

20. Kinds of Committees and Their Membership Composition

1. The Mainstream Executive Committee, whose members listed here-below are included, is hereby established at the Regional level:

A. The Deputy Head of the Government ------ ---------- chairperson;

B. The Head of Education Bureau --- member;

C. The Head of the Technical-Vocational and Enterprises Development Bureau --------- ---------- Member;

D. The Head of the Finance and Economic Cooperation Bureau ---------- member;

E. The Head of the Urban Development, Housing and Construction Bureau --------- ---------- member and secretary;

F. The Head of the Rural Land Administration and Use Bureau - Member;

G. The Head of the Agriculture Bureau ------ ---------- member;

H. The Head of Health Bureau ----- member;

ቀ. የክልሉ መምህራን ማህበር ሊቀ-መንበር------ ---------- አባል።

2. በዞን ደረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አባላት የተካተቱበት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡--

ሀ. የዞኑ ምክትል አስተዳዳሪ ---------- ሰብሳቢ፣

ለ. የትምህርት መምሪያ ኃላፊ ---------አባል፣

ሐ. የቴክኒክ-ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት መምሪያ ኃላፊ ---------- አባል፣

መ.የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር መምሪያ ኃላፊ ---------- አባል፣

ሠ. የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን መምሪያ ኃላፊ ---------- አባልና ጸሀፊ፣

ረ. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ ---------- አባል፣

ሸ. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ ሀላፊ ---------- አባል፣

ቀ. የግብርና መምሪያ ኃላፊ ..... አባል፣

በ. የጤና ጥበቃ መምሪያ ኃላፊ ---- አባል፣

I. The Chairperson of the Regional Teachers' Association ---------- member.

2. The executive Committee, whose members listed here-below are included, is hereby established at the zonal level:

A. The Zonal Deputy Administrator ---------- ---------- chairperson;

B. The Head of the Education Department ---- ---------- member;

C. The Head of the Technical-Vocational and Enterprises Development Department ------ ---------- member;

D. The Head of the Finance and Economic Cooperation Department -------- member;

E. The Head of the Urban Development, Housing and Construction Department ----- ---------- member and secretary;

F. The Head of Government Communication Affairs Department ------ member;

G. The Head of the Rural Land Administration and Use Department -------- ---------- member;

H. The Head of the Agriculture Department ..... member;

I. The Head of the Health Department -------- ---------- member;

ሀ. የዞኑ መምህራን ማህበር ሊቀ-መንበር ---------- አባል።

3. በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ደረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አባላት የተካተቱበት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተቋቁሟል፦

ሀ. የወረዳው ምክትል አስተዳዳሪ ወይም የከተማ አስተዳደሩ ምክትል ከንቲባ ------- ሰብሳቢ፣

ለ. የትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ---------- አባልና ጸሀፊ፣

ሐ. የጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ --- አባል፣

መ. የቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ---------- አባል፣

ሠ. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ኃላፊ --- ---------- አባል፣

ረ. በወረዳው ውስጥ የሚገኝ መሪ ማዘጋጃ-ቤት ዋና ስራ አስፈፃሚ ---------- አባል፣

ሰ. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ኃላፊ ---------- አባል፣

ሸ. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ሀላፊ ---------- አባል፣

ቀ. የግብርና ጽ/ቤት ሀላፊ ---------- አባል፣

በ. የወረዳው መምህራን ማህበር ሊቀ-መንበር ---- ---------- አባል።

J. The Chairperson of the Zonal Teacher Association ---------- member.

3. The executive committee, whose member listed here-below are included, is hereby established at the level of the Woreda/City Administration:

A. The Woreda Deputy Administrator/ Deputy mayor ---------- chairperson;

B. The Head of the Education Office ..... member and secretary;

C. The Head of the Health Office ... . member;

D. The Head of the Technical-Vocational and Enterprises Development Office ..... member;

E. The Head of the Finance and Economic C ooperation Office ---------- member;

F. The Chief Executive of Lead municipality found in the Woreda ---------- member;

G. The Head of Government communication Affairs' Office ---------- member;

H. The Head of the Woreda Rural Land Administration and Use Office -- member;

I. The Head of the Agriculture Office ..... member;

J. The Chairperson of the Woreda Teachers' Association ---------- member;

ተ. በከተማ አስተዳደር ሲሆን የዚሁ አስተዳደር ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት ሀላፊ ---- አባልና ጸሀፊ።

4. ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀፅ (3) መሰረት የተደራጀው ኮሚቴ በአንድ ወረዳ ስር በታቀፉ መሪና ንኡስ ማዘጋጃ-ቤቶች፣ በታዳጊ ከተሞች፣ በገጠር የቀበሌ ማዕከላትና በገጠር ቀበሌዎች ያሉትን ቀሪ ተግባራት ጭምር ያከናውናል።

21. የኮሚቴዎች የወል ተግባርና ኃላፊነት

በየደረጃው የተቋቋሙ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት የወል ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፦

1. በመምህራን የጋራ መኖሪያ መንደሮች ውስጥ የተገነቡ ቤቶችና የተካሄዱ የቤት መስሪያ ቦታ ድልድሎች ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት አግባብ ባላቸው አካላት የቅርብ ክትትል ስለመከናወናቸው ያጣራሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣ ይደግፋሉ፤
2. ለጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታው የቦታ ዝግጅትና አቅርቦት ያመች ዘንድ ከስፍራው ለሚነሱት ዜጎች በቅድሚያ የካሳ ክፍያ መፈፀም የአስተዳደሩ ጎጋዊ ግዴታ ሆኖ ሲገኝ ለዚሁ የሚያስፈልገው ተመጣጣኝ በጀት በክልሉ መንግስት አማካኝነት በንቃት እንዲያዝ አቅድ ያወጣሉ፣ ያስፈጽማሉ፤

K. In case of a city administration, the hhead of the Urban Development, Housing and Construction Service Office ---------- ---------- member and secretary.

4. The committee so organized in accordance with Sub-Art. (3) herein above shall carry out the rest of the duties existing in the lead and sub-municipalities, emerging towns, rural Kebele centers and the rural Kebeles embraced in the given Woreda.

21. Ccollective Duties and Responsibilities of the Committees

The Executive committees established at all levels shall, pursuant to this regulation, have the following collective duties and responsibilities:

1. Verify, supervise over and support that the houses constructed in the teachers' communal residential villages and the distributions of the plots of land for the construction of houses are carried out under the close follow-up of the pertinent organs in pursuance of the Regulation;
2. Where it has been found that it remains to be the lawful duty of the administration to disburse prior compensation payment for the citizens who might have been displaced from the place with a view to facilitating the preparation and provision of plots of land for the construction of the communal houses, formulate a plan for an active appropriation of a commensurate budget on the part of the Regional Government and cause its implementation thereof;

3. ከዞን፣ ከወረዳ ወይም ከከተማ አስተዳደሮች በኩል የሚላኩ የመኖሪያ ቤት ልማት አፈጻጸም ሪፖርቶችን በመገምገም ለበላይ አካላቱ ያቀርባሉ፤

4. ለጋራ መኖሪያ መንደሮች ግንባታም ሆነ ለልማቱ ተነሺዎች ካሳ ክፍያ የሚያስፈልገው በጀት እጥረት ያጋጠማቸው ዞኖችና ወረዳዎች ቢኖሩ እነዚህኑ በየጊዜው እየለየ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማስወሰን ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤

5. ራሳቸውን ችለው መኖሪያ ቤት የመስራት ፍላጎት ያላቸው መምህራን የጠየቁት ቦታ በአግባቡና በወቅቱ የተሰጣቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በየጊዜው እየገመገመ ተገቢውን አቅጣጫና አመራር ይሰጣሉ፣ አስተዳደራዊ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋሉ፤

6. በክልልና በዞን ከተሞች ውስጥ በሚገነቡት የጋራ መኖሪያ መንደሮች ለማንኛውም የክልሉ መንግስት ሰራተኛ የተቀመጠው የ20 በመቶ እድል ሳይነካ መምህራን ለብቻቸው 10 በመቶ የሚሆነውን ኮታ በአግባቡ መጠቀማቸውን በየደረጃው ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ፤

3. Evaluate and submit performance reports t senior officials with regard to the dwel house development to be sent by the zo Woreda or city administrations;

4. Should there exist zones and Wore encountering budget deficit required for compensation payment of construction communal residential villages or for perso displaced as the result of developme identify same from time to time and cause the to obtain additional financial support upo decision by the council of the regiona government;

5. Evaluate, from time to time, and provide appropriate direction and leadership in collaboration with the organ concerned with the matter, with a view to ascertaining that those teachers having a desire to construct their own dwelling houses are duly and timely provided with the land they have requested for and cause the taking of administrative measures of rectification thereof;

6. Follow up and evaluate at all levels that teachers duly utilize their 10% share solely, without prejudice to the 20% opportunity reserved for any regional government civil servants of the communal residential villages to be constructed in the regional and zonal cities;

7. በዚህ ደንብ ያልተሸፈኑ ሌሎች የአሰራር ክፍተቶች ሲያጋጥሙ የመፍትሄ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፣ ያስወስዳሉ።

22. ስለኮሚቴዎች የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርአት

1. በየደረጃው የተቋቋሙት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ስብሰባ ቀጥሎ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይካሄዳል፦

ሀ. ክልል-አቀፉ አቢይ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቢያንስ በሶስት ወር 1 ጊዜ፤

ለ. የዞን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ቢያንስ በሁለት ወር 1 ጊዜ፤ ና

ሐ. የወረዳ/ከተማ አስተዳደሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በወር አንድ ጊዜ።

2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የየደረጃው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

3. ከኮሚቴው አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ-ጉባኤ ይሆናል።

4. ማናቸውም ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ ከተገኙት የኮሚቴው አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በሚሆኑት አባላት ድምጽ ሲደገፍ ብቻ ነው። ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

7. Take and cause the taking of measures of solution when facing other working gaps, not covered in this regulation.

22. Meeting Time and Decision-Making Procedures of the Committees

1. The meeting of the executive committees established at all levels shall be carried out on the basis of the time schedule specified as follows:

A. the Region-wide Principal Executive Committee, at least once in three months;

B. the Zonal Executive Committee, at least once in two months; and

C. the Woreda/City Administration Executive Committee, once in a month.

2. Notwithstanding the provision of Sub-Art. (1) of this Article hereof, the chairperson of Executive Committees at all levels may convene an extra ordinary meeting where he finds it necessary to do so.

3. There shall be a quorum where more than half of the Committee's membership are present at the meetings.

4. Any decision shall pass only if it is supported by more than half of the Committee's membership showing up at the meeting; in case of a tie, however, the chairperson shall have a casting vote.

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

23. የመተባበር ግዴታና የወንጀል ኃላፊነት

1. ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ በማስፈጸም ረገድ የመተባበርና አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተጠየቀውን ማናቸውንም ድጋፍና እገዛ የመስጠት ግዴታ አለበት::

2. የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም መምህር በዚህ ደንብ ውስጥ የሰፈሩትን ድንጋጌዎች ተላልፎ የተመዘገበ ወይም ለመመዝገብ የሞከረ ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ ሂደቱን ያሰናከለ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ተጠያቂ ይሆናል::

3. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት ያጓተተ፣ ለአፈፃጸሙ እንቅፋት የሆነ ወይም ማናቸውንም ሌላ ተያያዥነት ያለው ችግር የፈጠረ የክልሉ መንግስት ወይም የተዋረድ አካላቱ ሹም፣ የስራ ሀላፊ ወይም ባለሙያ አግባብ ባላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል::

PART

MISCELLANEOUS PROVISIONS

23. Duty to Cooperate and Crimin Liability

1. Any person shall, with regard to th implementation of this regulation, have th obligations to cooperate and provide any support and assistance, where requested by the pertinent government organ.

2. Any teacher entitled for the benefit who has violated the provisions laid down under this regulation hereof and been registered or tried to do so or hindered the process in any other means shall be liable pursuant to the relevant provisions of the criminal law.

3. An appointee of the Regional Government or its hierarchically -structured organ, official/head or expert, who has obstructed the implementation of the provisions of this regulation without sufficient and lawful cause, become obstacle for its implementation or created any other difficulty shall be liable in accordance with the relevant provisions of the criminal law.

26. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

በዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ቢሮ ለደንቡ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

27. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሁለት አመትና ከዚያ በላይ ክልሉን ላገለገሉ መምህራን የነደፈውን የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥና የተገነቡ ቤቶች ድልድል መርሀ-ግብር በሶስት አመታት ጊዜ ውስጥ አጠናቅቆ ለመፈፀም እስከተወሰነበት እስከ 2012 በጀት ዓመት ማብቂያ ድረስ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
የካቲት 17 ቀን 2009 ዓ.ም
ገዱ አንዳርጋቸው
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ርእሰ-መስተዳድር

26. Power to Issue Directives

Without prejudice to other provisions of this regulation with regard to the powers vested in the Council of the Regional Government, the Education Bureau may issue specific directives for the full implementation of the provisions of this regulation.

27. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State until the end of the 2020 Ethiopian fiscal year , on which date it has been determined to fully accomplish the program devised for the delivery of plots of land for the construction of the dwelling house and the distribution of houses constructed for those teachers serving the Regional State for the period of two years and above.

Done at Bahir
Dar This 24th day of February, 2017
Gedu Andargachew
Head of Government of the Amhara National
Regional State